## እሁድ መጋቢት 11፥ 1997 (ማርች 20፣ 2005)

በፍኖተ ዲሞክራሲ ሬድዮ የቀረበ፤

## ማን ያውራ የነበረ (ቁ. 11)

## ኢሕአፓና ሀቀኛ ታሪኩ ።

ኢትኦጵ የተባለው መፅሔት በመጨረሻ ገፁ ላይ “መንገድ” በሚለው አምዱ በቅርቡ በቃለ መጠይቅ እንግዳ ብሎ ያቀረበው ኢትዮጵያዊ ይህን አስከፊ እውነታችንንና ጤና የምንለውን ትቶ ወደ ራሱ ዓለም የገባ ግለሰብ ቢሆንም የእብድ በመሰለ መልሱ ጤና ነን የሚሉትን ብዙዎችን አጋልጧል። በኔፐትዩን ሰማየ ሰማያት ተወለድኩ የሚለውና ራሱን ፕሮፌሰር ሲራጅ ብሎ የሚጠራው ይህ ግለሰብ የአባይ ውሃ የሚመጣው ከቤርሙዳ ሀይቅ ሲሆን በጎንደር በኩል ሄጄ አይቸዋለሁ ማለቱ ብቻ ሳይሆን ስለ ፖለቲካ ምን ታውቃለህ ብሎ ሲጠየቅ የሰጠው መልስ “ስለ ኢሕአፓ አውቃለሁ--ኢሕአፓዎች የደርግ አባል መሆናቸውን” የሚል ነው። ፕሮፌሰር ሲራጅ በሌላ ዓለም ውስጥ ነውና የሚፈርድበት የለም። ግን በአራት ኪሎ ቤተመንግስትና በቃሊቲም እስር ቤት ወይም በስደት ዓለም ሆነው ነጋ ጠባ ኢሕአፓን በተመለከተ የሚዋሹትን ግን አብደናል አይሉምና ሁሌም በዝምታ ማለፍ የሚቻል አይደለም። ኢሕአፓና ሀቀኛ ታሪኩ መጠበቅ አለባቸውና ነው።

ደግመን ደጋግመን ማን ያውራ የነበር ስንል ሀቅ ሞቶ ሳይቀበር፤የነበሩ ሞተው ሳያልቁ በሬ ወለደው አይከሰት ለማለት ነበር። ግን ልማድ ሆነና፤የራስን ፀያፍ ታሪክ መደበቁ አስፈላጊ ሆነና ውሸቴን ብተው ይበታትነኝ ያሉ ክፍሎች ዛሬም ሀሰትን ከማሰራጨት መታቀብ አቅቷቸዋል። በእስር ያሉ የደርግ ባለስልጣኖች ወንጀላቸውን አምነው ንስሀ ከመግባት ፈንታ የፈጁትን ኢሕአፓን እየወነጀሉ መቀጠሉን መርጠዋል።ለፍርድ ቤት እንዳናቀርብ ተከለከልን የሚሉት ሰነድ ለምሳሌ ኢሕአፓን በሀሰት እየወነጀለ ለቀውሱም ተጠያቂ ሊያደርግ የሚጥር ነው። ኢሕአፓ በከተማ የተካሄደውን ትግል በተመለከተ ከሁሉም በፊት ይህ ስህተት ነበር ብሎ የሚያምንበትን ተቀብሎ ይፋ ያደረገ ሲሆን በደርግ አባሎችና በሌሎቹም እየተደጋጋመ ያለው በከተማ ተኩስን የጀመረው ኢሕአፓ ነው የሚለውን ግን ከመጀመሪያው ሀሰት ብሎ በመረጃም ሲያሳይ ቆይቷል። ኢሕአፓ ገና አንዲት ጥይትም ሳይተኩስ ነበር ደርግ የአፈና ሰራዊቱን በየቦታው አሰማርቶ ሰላማዊ ትግሉን ለማፈን ሕዝብን መጨፍጨፉን የተያያዘው። በኢሰአማ ላይ፤ በበኢመማ ላይ፤ በስራ አጦች ላይ፤ በቦንጋና ብቸና አርሶ አደሮች ላይ፤በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኞች ላይ፤በብሄራዊ ቲያትር ሰራተኞች ላይ፤ ወዘተ እርምጃ የወሰደና የአስቸኳይ ጊዜ አፋኝ አዋጅ ያወጣ ድርግ ራሱ ነበር። የይፋ ሽብር በመስከረም 1969 ዝግጅት ተደርጎበት ከመታወጁ በፊት እነ አሊ ሙሳና ጌታቸው ሺበሺ ስንቱን ኢትዮጵያዊ በአስበ ተፈሪና ሌሎችም ቦታዎች እንደፈጁ ታሪክ መዝግቧል። የኢሕአፓ አልሞት ባይ ተጋዳይ መከላከል የተከሰተው ከዚህ ሁሉና ሽብርና ጦርነት ከታወጀበት በኋላ ነበር። የሰላሙ ሕዝባዊ አመፅ እየጋመ በነበረበትና ድልንም እያገኘ ባለበት ኢሕአፓ ቀድሞና ቸኩሎ ተኩስ አልጀመረም። እንዲያውም የሰላሙን ትግል ሂደት ጊዜ ለመስጠት ሰራዊቱን እንኳን በይፋ ሳያውጅ ቆይቷል፤በሰላም ሊታገል መፈለጉንም በሀገሪቷ ሙሉ ባሰራጨውም ፕሮግራም ይፋ አድርጓል።

ጆር ያለው ይስማ ነውና ለሀሰት ወሬ ብቻ የተቃኙ ጆሮዎች እስካልበዙ ድረስ የሀሰት መደጋገም አላዋቂን ለጊዜው ቢያደናግርም በረጅሙ ግን መጋለጡ አይቀሬ ነው። በክስ ላይ ያሉ የደርግ አባሎች ኢሕአፓ ተኩስ ከፈተብን፤ ከሻዕቢያም ከሶማሊያም አብሮ ዘመተብን ብለው ቢቀላምዱም ወርቅ ልጆቹን ለሀገር ሲል የገበረው ሁሉ፤ በሰራተኞች ቀን በሰላማዊ ሰልፍ ከሺ በላይ ወገኖቹ በግፍ ሲፈጁ የታዘበው ዜጋ ሁሉ ሀሰትና እውነቱን ለይቶ ያውቀዋል። ኢሕአፓ የሕዝብ እኩልነት ስላለ ሀገርን ሊገነጥል ፈለገ የሚሉት አቅዋሙን መረዳት ያቃታቸው ወይም ጭቁኖችን መደገፍ ሀጢያት የመሰላቸው መሆናቸውንም ደግመን ደጋግመን ያቀረብነው ነው። ኢሕአፓ አንኳን ዚያድ ባሬን ሊደግፍ ቀርቶ አባላቱና ደጋፊዎቹ በሶማሊያ

እስር ቤትና በሽለምቦድ “አምሀር” እየተባሉ ስቃይን የተቀበሉ መሆናቸውን ብዙ ሰው ያውቃል። የደርጉ ቁንጮ በሰጠው ቃለ መጠይቅ ለምሳሌ ኢሕአፓ ተኮሰብን፤ገደለን ወዘተ ብሎ ሲናገር ሕዝብ አስታጥቁን አታስጨርሱን አለን ብሎ መዋሸቱ ይታወሳል። ልጆቹን ሊጨርስ ማለት ነው! በዚህ ረገድ ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል። ኢሕአፓ ግን ተኩስን በመጀመር ሆነ በፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር በማበርና በመግጠም በመረጃ የሚታማ አይደለም። ወቅቱን በተመለከተ ደግሞ ሂስ መሳይ መርዛቸውን የሚረጩት ጥቂቶች አይደሉም። ኢሕአፓ ወጣቱን አስጨረሰ ይላሉ። ድርጅቱ ባመነበት ላመነበት ታገለ እንጂ ማገዶ የመሆን ልክፍት አልነበረውም። በደርግ እጅ ወድቆ መወገርና መሰቃየት፤ባዶ እጅን አራጅ ጦርን በሰለማማዊ ሰልፍ መጋፈጥ ወዘተ እስቲ ልሞክረው ተብሎ የሚጋባበት ጨዋታ እንዳልነበርና እንዳይደለ የነበሩትና የተሰቃዩት ያውቁታል። ትግል ሲባል ደግሞ የሞቀ የራት ግብዣና ፈንጠዝያ ሳይሆን ደም የሚፈስበትና የሚፈስለት ትንቅንቅ መሆኑን ዛሬም አስተማሪ መጠየቅ አሳፋሪ ነው። ኢሕአፓ ራሱ ያመነው ስህተት በከተማ መታገሉን ሳይሆን፤በአረመኔዎቹ ላይ በመከላከል መተኮሱን ሳይሆን የኃይል ሚዛ ሲቀየር በከተማው ትግል ከሚገባው ባለይ መቀጠሉን ነው። ዛሬ ትጥቅ ትግል የእንስሳ ነው ለማለት የደፈሩትም ሆኑ ኢሕአፓን በሽብር ክሰሱልን ብለው ነፈሰ ገዳዩን አገዛዝ የሚማጠኑትም ቢሆኑ በወቅቱ ፀረ ደርግ ሰላማዊ ትግል ሊያካሂዱ ቀርቶ በይፋም በምስጢርም የደርጉ አማካሪና ጋሻ ጃግሬ እንደነበሩ ደግሞ አልረሳንም።

ኢሕአፓ ገና ከጠዋቱ ከወያኔ ልገንጠል አላማ ጋር ተፃርሮ ታገለ እንጂ ስልጣን በቶሎ በሚል ከገንጣይ ኃይሎች ጋር አላበረም። የኤርትራ ችግር በሰላማዊ መንገድ ይፈታ አለ እንጂ ከሻዕቢያ ለማበር ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ ባለ 300 ገፅ መፅሀፍ ፅፎ አላሰራጨም። ወያኔም በትግራይ በኢሕአፓ ላይ ጦር ከፈተ እንጂ ኢሕአፓ ችሎታና አቅሙም እያለውም ቢሆን በወያኔ ላይ የጦር አዋጅ አላሰማም። አቅዋሙን ግን፤ ወያኔ ትግራይ ይገንጠል የሚለውን መቃወሙን ግን በይፋ አቅርቧል። ኢሕአፓ የመጨረሻ ግቡ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው፤ ሀገርንም ሸጦ ለቤተመንግስት መብቃት ቢል ኖሮ ደግሞ ችሎታ አልባ የወያኔ መንጋ ከደረሰበት መድረስ ባልተሳነውም ነበር። አዲሱ ትውልድ በዕድሜና በጊዜ የተነሳ ትላንት የደርግ ሀሰት፤ዛሬ ደግሞ የመለስ አገዛዝ ቅጥፈት እየወረደበት ታሪክን በተሳሳተ መንገድ እንዳይረዳ መከላከል ቢያንስ የሰማዕታቶቻችን ደም ግድ የሚለው ተልዕኮ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ነበርን፤እናውቃለን ወዘተ እያሉ መፅሐፍ የሚፅፉ ብቅ ብቅ እያሉ ናቸውና በየመፅሀፋቸው እያሰፈሩ ያሉትን ሀሰት ማጋለጡ ለእኛ የግድ ይሆናል። በካናዳ ሀገር የተሸለመ አንድ ፀሀፊ ነኝ ባይ ኢትዮጵያዊ ለምሳሌ በሀረር ጅጅጋ የኢሕአፓ አባል ሆነሃል ብሎ ሲነገርህ አሌ ካልክ እዚያው በጥይት ትገደል ነበር ሲል ሳያፍር በመፅሐፉ አስፍሯል። ነበር ነበርኩ ብሎ ከፊል ልብወለድ የደረሰውም ሻምበል ደግሞ የሌለ ሰነድ ፈጥሮ ሶማሊያ ኢትዮጵያን ስትወር ኢሕአፓ በከተማ ለሚገኙትና ሻምበሉ ገዳይ ቡድኖች ለሚላቸው የሰጠው ትዕዛዝ “ማንኛውንም የመንግስት ድርጅትማቃጠል፤በቀበሌ ተመራጮች ላይ ርምጃ ማፋጠንና በየጊዜው ቢያንስ አንድ ወይም ሁለት መምታት” የሚል ነበር ሲል መረጃ አሳየ ባይ የለም ብሎ ዋሽቷል። ታሪክና ሀቅ ብሎ በፃፈውም ውስጥ መንግስቱ ኃይለ ማርያምን ለመግደል በአዲስ አባባ ተሰብስበው የወሰኑ ብሎ ስም ዝርዝር ሲያቀርብ የመኢሶኑን አመራር አባል ሟች ደስታ ታደሰንም እንደ ኢሕአፓ አድርጎ አቅርቦታል። ሌሎች ደግሞ ድርጅቱ ያልወሰደውን አቅዋም በኤርትራ ጥያቄ ላይ ወስዶ ነበር ወዘተ እያሉ ከመፃፍ አልፈው የፃፉትን ለሕዝብ ሲያቀርቡም መድረኩን ወደ ኢሕአፓ ማውገዣ ለመለወጥ ሲጥሩም እንደነበር በቦታው የተገኙት ታዝበዋል።

ይህ ሁሉ ፀረ ኢሕአፓ ዘመቻና ርብርብ የሚካሄደው ደግሞ አገዛዙም ሆነ አጫፋሪዎቹ ድርጅቱ የለም፤ ህልውናው አጠያያቂ ነው በሚሉበት ወቅት መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም። ትላንትም ሀነ ዛሬ ለተራ ሹመትና ጨቋኞች ለሚያቁለጭልጩት ሳይሸነፍ የሕዝብንና የሀገርን ጥቅም አስቀድሞ የታገለውና እየታገለው ያለው ኢሕአፓ ከዓመታት በፊት የትግል ታሪኩን ገምግሞ ስህተት ያለውን ተቀብሎ ግለ ሂሱን ለሕዝብ ግልፅ ያደረገ ብቸኛ ድርጅት ነው። ሀገርን የሸጡ፤ ከአረመኔዎች ጋር ሆነው ብዙ ሺ ወርቅ ዜጋን የጨፈጨፉ፤ ሀገርን ያስገነጠሉና ዛሬም እየበደሉ ያሉት ሁሉ ሕዝብን ይቅርታ በሚገባ ሲጠይቁ አልሰማንም። ይባስ ብለው በኢሕአፓ ለይ መረባረብን መርጠዋል። ትላንትም ዛሬም የአገዛዙ የምስጢር አርበኛ ሆነው በሕዝብ እየቀለዱ በተጋለቢጦሽ ኢሕአፓን መወንጀል ይቀናቸዋል። ድርጅቱ ለህብረት

ትግል ባለው አቅሙ ሲዋደቅ የህብረቱን ጥረት የሚያደናቅፉት እነሱ ሆነው ሳለ ጥፋታቸውን በኢሕአፓ ላይ ያላክካሉ፡፡ ኢሕአፓ ባይኖር ኖር መደበቂያቸው ምን ይሆን ነበር ያሰኛል! ኢሕአፓ የዚህ ሰፊ የሀሰት ዘመቻ ተጠቂ የሆነው ለሀገርና ለሕዝብ ጠላቶችና ለእበላ ባዮች አላመች ስላለ ነው፡፡ባዕዳን ድግሞ በመጥፎ ዓይን ያዩት ለትዕዛዛቸው እንደ ወያኔ ተቀባይና አሽርጋጅ ባለመሆኑና የሀገርን ጥቅም አሳልፎ ባለመስጠቱ ነው፡፡

• ኢሕአፓ ከደርግ አገዛዝ የተጋጨው ስልጣን የሕዝብ ነው፤ዴሞክራሲ ለጭቁኖች አለገደብ በማለቱና የባዕዳንን ቁጥጥር በመቃወሙ ነው፤
• ኢሕአፓ ከወያኔ ጋር የተጋጨው እነ መለስ ዜናዊ ትግራይም ሌላውም ይገንጠል፤ኢትዮጵያ ትበታተን ሰላሉ ነው፤
• ኢሕአፓ ከእነ ሻዕቢያ የተጋጨው ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት የሚውን አቅዋማቸውን አልቀበል ሰላላቸው ነው፡፡
• ከሱዳን፤ከሊቢያ፤ከአሜሪካ፤ከእንግሊዝ፤ ከቻይና ወዘተም በአስፈለገበት ወቅት የተለየነው አቅዋማቸው ሀገርን ሲጎዳ ባየ በት ጊዜ ነው፡፡

ማን ሆናችሁ የሚሉ ነበሩ፤ዛሬም ይኖራሉ፡፡ ኃይል ያላቸውን ለምን ተጋፈጣችሁ የሚሉ ነበሩ፤ዛሬም አሉ፡፡ እንደ እነ መለስ ሀገርን ክዶ መጠቀም ነው የሚሉ ነበሩ፤ዛሬም አሉ፡፡ ይህ ግን የኦሕአፓ መስመርና እምነት አልነበረም፡፡ ዜዴና ስልት አስፈላጊ ቢሆንም ሀገርን አጥፋልኝ ሲል እሺ ብሎ ክብሪት መለኮስ ዘዴ ወይም ብልጥነት ሳይሆን ባንዳነት ነው፡፡ የሙሶሊኒን ኃያልና ወራሪ ጦር እየተዋጉ የተሰዉት አርበኞች ለእኛ አርአያ ሲሆኑ ባንዶች ደግሞ ለእነ መለስ ቅርብ ናቸው፡፡ ልዩነቱ እዚህ ላይ ነው፡፡ የመለስ መንጋ ለስልጣን ሲሮጥም በኢሕአፓ ሬሳ ላይ መረማማዱ አለምክንያት አልነበረም፡፡ ኢሕአፓ በሰላማዊ መንገድ ልታገል ዝግጁ ነኝ እያለ በሰበብ አስባቡ ያገደውና ህገ ወጥ ያለው አለምክንያት አልነበረም/አይደለም፡፡ ኢሕአፓን የቡድንኑን ማንነትና አሰራር ጠንቅቆ ከማወቁ ሌላ በነፃ መድረክ የመለስን ቡድን እርቃኑን እንደሚያወጣው ቢያንስ በቡድኑ የታመነበት በመሆኑ ነው፡፡ ቡድኑ ለስልጣን ሲበቃና ገዢ ነኝ ሲል ኢሕአፓ ህገ ወጥ ነህ ሲል ተቃውሞታል፡፡ ወያኔ በወደደው ቦይ ሊፈሱ የተነሱትንና በደርግ ዘመን በለመደባቸው አድር ባይነት ልጆቼ ያሉትንም አደብ እንግዛ ብሎ መክሯል፡፡ የመደራጀት መብትን ባይፃረርም በብሄረሰብ መካለሉ ለዘለቄታው ጠቃሚነቱ ለእነ ወያኔ ነው ብሎ አሳስቧል፡፡ የኤርትራንም ችግር ለመፍታት የተወሰደውን እርምጃ ጉዳትም ከመጀመሪያው ገልጦ ነበር፡፡ የኦሮሞን ህዝብ መብት የሚጠይቁትን እየደገፈ የዚህን ህዝብ ኢትዮጵያዊነት የሚክዱትን ተቃውሞአቸዋል፡፡ከመለስ ዜናዊ ጋር ገጥመው ዛሬ ግን ለስደት የበቁትንም ገና ከያኔው ስህተት እየፈፀማችሁ ነው ብሏቸው ነበር፡፡ ባዕዳኑ የመለስን አገዛዝ ስላወደሱ ቁሻሻውን ሌላ ስም መስጠት አይሆንልኝም ብሎም በአቅዋሙ ፀንቷል፡፡ የወያኔ ወዳጆች እነ ሱዳንም ኢሕአፓ ስደተኞችን ለወያኔ አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ ለእስር የበቁት የኢሕአፓ መሪዎችና አባላትም እነሆ እስከዛሬም ደብዛቸው ጠፍቷል፡፡

ዛሬ የአቅዋም ፅናት መቀለጃ የመሰላቸው ሲጮሁ ቢሰሙም ነፋስ በነፈሰና ጅብ በጮኸ ቁጥር ድርጅቱ ሽብረክ እያለ ቃል ኪዳኑን ከትብያ የሚጥል አይደለም/አልነበረም፡፡ ምርጥ መኮንኖች የሕዝብን ትግል አደናቅፈው ስልጣን ሲጨብጡ ኢሕአፓ ለሹመት በመቋመጥ፤ላማክር ብሎ በመለመን አፋኙን ቡድን ዴሞክራሲያዊ ብሎ ሕዝብን አልካደም፡፡ ስለዚህም አይነጋ መስሏቸው ታሪካቸውን ያበላሹት ዛሬ ኢሕአፓ በሞተ በተቀበረ ባይ ናቸው፡፡ መልካቸውን ቀይረውና ጭምብል አጥልቀው ተቃዋሚም ሀገር ወዳድም ነፃ አውጪም ነን እያሉ በዚሁ ሽፋን በመጠቀምና መጠጊያም መሸሸጊያም በማግኘት ነጋ ጠባ በኢሕአፓ ላይ የሀሰት ዘመቻቸውን አጧጥፈዋል፡፡ ድርጅቱን በሆነ ባልሆነ መክንያት የከዱና ከመክዳታቸውም በፊት ጉዳይ ያደረሱ፤ ወይም ዛሬ ፀረ ሕዝብ ከሆነው አገዛዝ ጋር ሆነው ሕዝብን መበደሉን የተያያዙት ሁሉ በኢሕአፓ ላይ መዝመታቸው ቀጣይ ክስተት ሆኗል፡፡ ኢሕአፓ ከቂም በቀል ይልቅ ይቅር ለእግዜር ይቅደም በሚለው አቅዋሙ መሰረት ሕዝብን ይቅርታ የጠየቀና ከሕዝብ ጎን የቆመ ሁሉ የትግሉ አካል ይሆናል ከማለት አልተቆጠበም፡፡ የጥፋት ጥፋት በወንጀልና በጥፋት መቀጠል ነውና፡፡ ኢሕአፓ ዛሬም ቢሆን ለሰፊው ሕዝብ መብትና ደህንነት የሚታገልና ዴሞክራሲ ሲለም ህብረተሰቡን በስፋት የሚጠቅም

የሚያገለግል ዴሞክራሲ ማለቱ ስለሆነ-- ራሱን ሶሻል ዴሞክራት ያለም በመሆኑ-- የምርጦችን የበላይነት ስርዓት ሊያሰፍኑ ከሚጥሩ ጋር ሁሉ መሰረታዊ ቅራኔ አለው፡፡ ባህልና ቅርስ ይጠበቅ በሚለው የሚያምን ቢሆንም የየወደቀን የጭቆና ስርዓት መልሰው ሊያሰፍኑ ከሚጥሩት ጋር በአንድ ጎራ አይሰለፍም፡፡ አንዱን ጨቋኝ አገዛዝ በሌላ ለመተካት ከሚፈልጉ ጋር አይሰምርም፡፡

በተደጋጋሚ በኢሕአፓ ለይ የሚሰነዘረውን "ሀገር አስገነጠለ " ክስ በተመለከተ ደግመን ደጋግመን ሀቁን ያሰፈርን ቢሆንም ዛሬም ይህንኑ የሀሰት ክስ የሚያሰሙ አልጠፉም፡፡ ኢሕአፓ ስልጣን ያያዘ መንግስት ሆኖ፤ፌዴሬሽን አፍርሶ፤አርበኞችን አግልሎ ፤ ኋላቀር ስርዓትን አስፍኖ ወይም የሰላሙን መንገድ እምቢ ብሎ፤ ወጣቶችን በአደባባይ አንቆ፤በትምክህት ሕዝብን ፈጅቶ ወዘተ ለጠባቦች መንገድ ያመቻቸ አልነበረም፡፡ ኢሕአፓ ለሕዝብ እኩልነትና መብት በመታገል ሀገርን በአንድነት ሊያቆይ ጣረ እንጂ የጨቋኞችን ትምክህት ተጋርቶ ሕዝብን የባለይና የበታች ወይም መርጥና የገዢ ብሎ በመፈረጅ ለክፍፍል ድልዳል አለባጀም፡፡ ወያኔ ልገንጥል ሲል፤ሌሎችም በዚሁ መስመር ካልሆነ መፍትሂ የለም ሲሉ ቀደም ሲል በርዕዮቱ የተነሳ ይዞት የነበረውን አቅዋምም በጊዜ በማስተካከል ለሕዝብ አንድነት እንጂ ለመገንጠል እታገል ከማለቱ ሌላ የኤርትራ ጉዳይ ደግሞ በፌዴራላዊ ትስስር እንዲፈታም ጥሪ አቀርቦ በተጨባጭም ተንቅሳቅሶ ነበር፡፡ ኢሕአፓ ከጠባብ ብሄርተኞች ጋር ተፋጦ ሲታገልና ጦር ሲዘምትበት ዛሬ የሀገር አንድነት አባወራ ነን ባዮች የት እንደነበሩ መጠየቅ አግባብ ያለው ይሆናል፡፡ ኢሕአፓ ብሄረሰብ አቀፍ ሆኖ በመገኘቱ በጣበቦችም በትምክህተኞችም ሲወገዝ እንደነበርም አንረሳውም፡፡ ይህ አንግዲህ ሀቅ እንነጋገር ከተባለ ግልፅ የሚሆን ነው፡፡ ኢሕአፓ ባሻዕቢያ ተመሰረተ ፤ የግንጠላን ሂደት ደገፈ ወዘተ እያሉ ሀሰትን ሀቅ ብለው ሊቀጥሉ የማሉትን መመለስ ባንችል አንኳን ህሊና ያለውን ከሀቁ ማስተዋወቅ ግዴታችን ነው፡፡ ኢሕአፓን እየከሰሱ ግን ከገንጣይና አስገንጣዩ አገዛዝ ጋር አብረው የቆሙትን ደግሞ የሌባ ዓይነ ደረቅ ብለናቸው እናልፋለን፡፡

ኢሕአፓ የሀገርን አንድነት ከሕዝብ መብትና አንድነት ጋር አጣምሮ የሚያይ በመሆኑ ድርጅቶችን ስለተቃዋመ ሕዝብን በጅምላ ጠላት ብሎ ከሚሰይሙ ጋር ተጋጭቷል፤ዛሬም ይቃረናል፡፡ የአማራ ሕዝብ ጨቋኝ ነው ጠላታችን ነው ካሉት ጋር ትላንትም ዛሬም ተፃራሪ ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ ሻዕቢያን አንወድምና የኤርትራ ሕዝብ ጠላታችን ነው ከሚሉትና ኤርትራውያን አላግባብ ከኢትዮጵያ በወያኔ ሲባረሩ ከደገፉት ጋርም ልዩነቱን በይፋ ገልጧል፡፡ የመለስ ቡድን ፀረ ኢትዮጵያ ሆኗልና፤ቡድኑ ለተገራየ ቆሜያለሁ ይላልና፤ እበላ ባዮች የትግራይ ተወላጆች ይ ሀይ ብለውታልና ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ጠላታችን ነው ሊሉ የተነሱትን ሆነ የሚሉትን ደግሞ መሰረታዊ አቅዋማችንም ሆነ ስንታገል አቅፎን የነበረው ሕዝብ ውለታና የሰማዕታቶቻችንም ደም አይፈቅዱልንም ብለናቸዋል፡፡ በዚህ ሁሉ የምንለያቸው የተሳሳተ አቅዋማቸውን ከመቀየር ፈንታ ወይም በጥሞና ውይይት ከማድረግ ይልቅ በአሉባልታ ስርጭት ተሰማርተው ለመለስ አገዛዝ የቅጥፈት ወፍጮ እህል አቅራቢ ይሆናሉ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገር ቤት እየታተሙ ያሉ አንዳንድ መፅሀፍት ፀሀፊዎች ሀላፊነት በጎደለው መንገድ ያልተባለን ተባለ፤ያልተደረገን ተደረገ ፤ያልተፃፈን ተፃፈ እያሉ በመን ደፍሮ ሊከሰኝ መንፈስ የሚያሰፍሩት ሁሉ ለትዝብት የሚዳርግ ሆኗል፡፡ ስለ ኢሕአፓ ለመፃፍ በድርጅቱ ገብቶ መውጣት ሳይሆን ድርጅቱን ጠንቅቆ ማወቅን ወይም ለማወቅ ምርምር ማካሄድን ይጠይቃል፡፡ ይህ ሳይሆን ግን አወቅኩ ነበርኩ ብሎ ያው እጅ እጅ ያለውን ቅጥፈት በኢሕአፓ ላይ ማዠጎድጎዱ የሚጠቅመው ለወያኔና ንስሐን ለፈሩ ለፀረ ሕዝቦች ብቻ ነው፡፡
ኢሕአፓ ህያው የሆነ የሕዝብ ቅርስና የታሪክ አምድ ነውና ያልነበረ አያውራ፤ያላየ አይመስክር እያለ በአስፈላጊው ጊዜና ሁኔታ ሁሉ ማን ያውራ የነበረ ማለቱ አይቀሬ ነው፡፡